

ወልቂጤዩንቨርስቲ

የማህበረሰብ እና ስነ ሰብ ኮሌጅ የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል

`` አለሜ ሲትኮም ድራማ ከሲትኮም ድራማ ባህሪያት አንፃር ትንተና ``

በ

ጅላሉ አባተ

ሚያዚያ/2017ዓ.ም

`በ

ጅላሉ አባተ

የጥናቱ አማካሪ

መምህርት ቤተልሄም አንጃ

በማህበራዊ ሳይንስ እና ስነ ሰብ ኮሌጅ ለቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል

ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ

የአማካሪው ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በወልቂጤ ዩኒቨርስቲ የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ድግሪ ማሟያ መስፈርት መሰረት ድጋፍ የተደረገለት መሆኑን አረጋግጣለሁ።

የአማካሪው ስም_____

ፊርማ_____

ቀን_____

ይህ ጥናት በ ጅላሉ አባተ አለሜ ሲትኮም ድራማ ከሲትኮም ድራማ ባህሪያት አንፃር በሚል ርዕስ የሰራዉን የመጀመሪያ ድግሪ ሚሟያ ፅሁፍ የዩኒቨርስቲውን ጥራት እና ደረጃ ያሟላ ለቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ተቀባይነት መሆኑን ማረጋገጫ ነው።

ይህም በፈታኝ ኮሚቴ ተረጋግጧል።

ፈታኝ አንድ

ስም_____

ፊርማ_____

ቀን_____

ፈታኝ ሁለት

ስም_____ _____

ፊርማ_____

ቀን_____

ምስጋና

ይህንን ጥናታዊ ፅሁፍ በምሰራበት ወቅት በትዕግስት እና በትጋት በፍፁም ትህትና ስህተቴን በማረም በማስተካከል ጠቃሚ ሀሳብ በመስጠት ከፍተኛ ድጋፍ ላደረገችልኝ አማካሪዬ መምህርት ቤቱሊሄም አንጃ ምስጋናዬ እጅግ ከፍ ያለ ነው ። በመጨረሻም ከፈጣሪ በታች ሙሉ ህይወታቸውን ገብረው እዚህ እንድደርስ ብዙ ዋጋ ለከፈሉልኝ በቃላት ለማልገልፃቸው ለአባቴ አባተ ሙሀመድ እና ለውድ ለእናቴ እንዲሁም የራሷን ህይወት ሳትኖር ለኔ ለኖረችው ውድ እህቴ ሙሉወርቅ አባተ በተጨማሪም ለዉዱ የግቢ ጓደኞቼ እና ለዉዱ የትምህርት ክፍል ጓደኞቼ ኦላና ተስፋዬ እና ሄርሜላ ምልክት ፈጣሪ ዕድሜ እና ጤና ይስጣችሁ ።

አበርክቶ

እሷ ሳትኖር ለኔ ለኖረችው የእርሷን ህይወት ትታ እኔ ህልሜን እድኖር ለረዳችኝ ላገዘችኝ፤የእነሷን ፍላጎት ሳታሳካ ለኔ በመጨነቅና በማሰብ ላስተማረችኝ ውድ እናቴ እንዲሁም ለወንድሜ ይሁንልኝ ።

አጠቃሎ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ "አለሜ"ሲትኮም ድራማ ከሲትኮም ድራማ ባህሪያት አንፃር የቀረበ ነው።በጥናቱም ዉስጥም የሲትኮም ድራማ ባህሪ የሆኑትን የገፀ ባህሪያት ቅርፆች አጭር ማህበራዊ አስተያየት ከተመልካች ጋር የቀጥታ ግኑኝነት መኖር መዋቅር ግጭት እንዲሁም ቀልድ እና የመሳሰሉት የሲትኮም ድራማ ባህሪያትን በመተንተን አለሜ ድራማን ከሲትኮም ድራማ ባህሪያት አንፃር ተንትነዋል።ይህንን ርእስ መሰረት አጥኚዉ አይነታዊ የምርምር ዘዴ ተጠቅሞ የጥናት ወረቀቱን አጠናክሯል።አይነታዊ የምርምር ዘዴ ዉስጥ የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ቢኖረዉም አጥኚዉ በመረጃ መሰብሰቢያነት የተጠቀመዉን በዋነኝነት ምልከታ እና መፅሀፎች በመጠቀም የአለሜ ሲትኮም ድራማ የነበረዉን የሲትኮም ድራማ ባህሪያትን በመተንተን ገልጿል።አለሜ ሲትኮም ድራማ ላይ ያሉ የሲትኮም ድራማ ባህሪያትን በመተንተን ምን እንደሚመስል ትንተና አድርጓል።። በትንተናዉም ወቅት ሙሉ ለሙሉ በሚባል ደረጃ የሲትኮም ድራማ ባህሪያትን የሚያሟላ ሆኖ ተገኝቷል።

1. ማውጫ ገጽ

2. ምእራፍ አንድ

3. 1.መግቢያ 1

4. 1.1 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት 3

5. 1.2 የጥናቱ አላማ.....3

6. 1.2.1 የጥናቱ አቢይ አላማ.....3

7. 1..2.2 የጥናቱ ንዑስ አላማ.....3

8. 1.3የጥናቱ ጠቀሜ.....3

9. 1.5 ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች 3

10. 1.6 የጥናቱ ወሰን.....4

11. 1.7 የጥናቱ ዘዴ.....4

12. 1.8 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች 5

13. 1.9 የጥናቱ አደረጃጀት 5

14. ምዕራፍ ሁለት

15. 2 ክለሳ ድርሳን 6

16. 2.1 የሲትኮም ድራማ ምንነት 7

17. 2.2 የሲትኮም ድራማ ባህሪያት 8

18. 2.2.1 መዋቅር.....8

19. 2..2.2 ቀልድ.....9

20. 2.2.3 ገፅታዎች 9

21. 2.2.4 የገፀ ባህሪያት ቅርፆች.....10

22. 2.2.5 ግጭት 10

23. 2.2.6 ጥራት 10

24. 2.2.7 የተመልካች ተሳትፎ 11

25. 2.2.8 ማህበራዊ አስተያየት 11

26. 2.2.9 ርዝማኔ 12

27. ምዕራፍ 3

28. 3.የመረጃ ትንተና 12

29. 3.1 የአለሜ ሲትኮም ድራማ ታሪክ በአጭሩ 12

30. 3.2 መዋቅር ወይም ትእይንት ቅርፀት 13

31. 3.3 ቀልድ 14

32. 3..4 ገፅታዎች 16

33. 3.5 የገፀ ባህሪያት ቅርፆች.....18

34. 3.6 ግጭት.....19

35. 3.7 ጥራት.....20

36. 3.8 ማህበራዊ አስተያየት 21

37. 3.9 ርዝማኔ.....21

38. 3.9.1 ከተመልካች ጋር የቀጥታ ስርጭት መኖር 22

39. 4 ምዕራፍ አራት

40. 4.1ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሀሳቦች.....23

41. 4.2 ማጠቃለያ 23

42. 4.3 የመፍትሔ ሀሳቦች 23

43. ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው 23

44. ዋቢ ጽሁፎች.....24

ምዕራፍ አንድ

1. መግቢያ

ኮሜዲ አስቂኝ የስነ-ጽሁፍ፣ የፊልም እና የአፈጻጸም ዘውግ ሲሆን ተመልካቾችን በቀልድ ለማዝናናት እና ለማስደሰት ያለመ ነው። ብዙውን ጊዜ የሰውን ባህሪ፣ የህብረተሰብ ደንቦችን ወይም የተለዩ ሁኔታዎችን ለማጉላት ማጋነንን፣ ምፀትን፣ ፌዝ እና ብልግናን ያካትታል። እንደ አልፈርድ አገላለፅ ኮሜዲ የተለያዩ ቅርጾችን ሊወስድ ይችላል፣ የቁም ስልቶችን፣ ፊልሞችን፣ የቴሌቭዥን ፕሮግራሞችን፣ ቴአትሮችን እና ስነፅሁፍን ጨምሮ።(alferd jon,2008)

" ኮሜዲ የተለያዩ ዘዉጎች ያሉት ሲሆን ከእነሱም ዉስጥ አንዱ ሲትኮም ድራማ ነው። ሲትኮም ድራማ አንድ የኮሜዲ ድራማ ዘውግ ሲሆን ገጸ-ባህርያቱ ተመሳሳይ ቦታ ላይ የሚኖሩ ተደርገው አልያም ተመሳሳይ ቦታ ላይ ተደርገው ይሳላሉ። ቃለ ተውኔታቸው የተመረጡ ሳቅን የሚያጭሩ በሳል መሆንም አለባቸው። ‹‹ይህ የኮሜዲ ዘውግ አጀማመሩ በሬድዮ የነበረ ሲሆን አሁን ላይ ግን በቴሌቭዥን ቻናሎች የሚተላለፍ እጅግ ተወዳጅነትን እያገኘ ያለ የቲቪ ዘውግ ነው››(alferd jon 2000) በማለት ሀሳቡን አስቀምጧል"።

ይህ የድራማ ዘውግ አይነት ከድርጊት ይልቅ ቃለ-ተውኔት ይበዛዋል። የተመልካች ሳቅ በመቅረጽ ድምጹ ተቀርጾ ከሚያስቀው ቃለ-ተውኔት ድርጊት ጋር ይለቀቃል (sitcom) ሲትኮም (situation comedy) ከሚለው የተገኘ ምህጻረቃል ነው። ሲትኮም ድራማ፣ ብዙ ጊዜ "ድራማ" እየተባለ የሚጠራው የሁለቱም ሁኔታዊ ኮሜዲ (ሲትኮም) እና ድራማ ክፍሎችን የሚያጣምር ዘውግ ነው።

የሲትኮም ድራማ ገፀ ባህሪያት ብዙ ጊዜ የተወሳሰቡ እና ከጊዜ ወደ ጊዜ ጉልህ እድገት የሚያደርጉ ናቸው፣ ይህም ከተመልካቾች ጋር ጥልቅ ስሜታዊ ግንኙነቶችን ለመፍጠር ያስችላል። የሲትኮም ድራማ ገፀ ባህሪያት ብዙ ጊዜ የተወሳሰቡ እና ተጨባጭ ያልሆኑ እንዲሁም በየጊዜዉ የሚቀያየሩ ናቸዉ። ገፁ ባህሪዮቹ ከተመልካች ጥልቅ ቁርኝት ያላቸዉ ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ እና እንደ ሁኔታዉ የሚቀያየሩ ናቸው። አልፈርድ ስለ ሲትኮም ድራማ ሀሳብ ምን ላይ እንደሚያጠነጥን እንደሚከተለው አስቀምጦታል "የሲትኮም ድራማ ሀሳብ የእውነተኛ ህይወት ጉዳዮች፡- የታሪክ መስመሮቹ እንደ ግንኙነቶች፣ የቤተሰብ

ተለዋዋጭነት፣ የአእምሮ ጤና ወይም ማህበራዊ ተግዳሮቶች ያሉ የእውነተኛ ህይወት ጉዳዮችን ሊፈቱ ይችላሉ"(alferd jon.2008) በማለት ገልፆታል ።

እንደ ደልተን አገላለፅ ሲትኮም ድራማ በተለምዶ አስቂኝ ሁኔታዎችን እና ውይይትን ያሳያል ነገር ግን ከባድ ጭብጦችን፣ የባህርይ እድገትን እና ስሜታዊ ጥልቀትን ያካትታል። ይህ ዘውግ በቀልድ እና በአሳዛኝ ታሪ

መካከል ሚዛን እንዲኖር ያስችላል፣ ብዙ ጊዜ ውስብስብ ግንኙነቶችን እና ግላዊ ፈተናዎችን ያስሳል፣ የሲትኮም ድራማ ታሪኮች በእውነት ላይ የተመሰረቱ ሲሆን ማህበራዊ ተግዳሮቶች ላይ በማተኮር የሚቀርቡ ናቸው።ሲትኮም (አጭር ለሁኔታ አስቂኝ ወይም ሁኔታዊ ኮሜዲ) ለሬዲዮ እና ለቴሌቭዥን የሚዘጋጅ የአስቂኝ ዘውግ ነው፣ ይህም ተደጋጋሚ ገጸ-ባህሪያትን እንደ ቤት፣ የስራ ቦታ ወይም ማህበረሰብ ያሉ አስቂኝ ሁኔታዎችን በወጥነት ሲሄዱ ያሳያል።(daltons 2012)

በሀገራችን ይሄ የድራማ ዘውግ እጅግ ተወዳጅነትን እያገኘ ያለ እና በሰፊው እየተሰራበት የሚገኝ ዘውግ ነው። ሀገራችን ላይ የተሰሩ እና እየተሰሩ ከሚገኙ ሲትኮም ድራማዎች መሃል አንዱ "አለሜ" ሲትኮም ድራማ ነው። "አለሜ" ተከታታይ ሲትኮም ድራማ ዕዝራ-ኢንትርቴመንት ከEBS ቴሌቬዥን ጋር በመተባበረ ዘወትር ማክሰኞ ከምሽቱ 3፡00 የሚተላለፍ ነው። በመሆኑም አጥኝው ከላይ በጠቀሰው መሰረት ማለትም ከሲትኮሞ ድራማ ባህሪያት አንጻር አለሜ ሲትኮም ድራማን ይገመግማል።

1.1 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አጥኚዉ ይህንን ጥናታዊ ፅሁፍ ለማጥናት በዋነኝነት ያነሳሳዉ ምክንያት "አለሜ" ሲትኮም ድራማ ከሲትኮም ድራማ ባህሪያት አንፃር የተሰራ ምንም አይነት ጥናታዊ ፅሁፍ ስለሌለ "አለሜ" ሲትኮም ድራማ የሲትኮም ድራማ ባህሪያት ያሟላ ነዉ ወይ?የሚለዉን ሀሳብ ለማስቀመጥ እና ባህሪያቶችን በግልፅ ለማሳየት ነዉ።

1.2 የጥናቱ አላማ

1.2.1 የጥናቱ አቢይ አላማ

የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ አቢይ አላማ "አለሜ" ሲትኮም ድራማን ከሲትኮም ድራማ ባህሪያት አንፃር መተንተን ነው።

1.2.2 የጥናቱ ንዑስ አላማ

የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ንኡስ አላማ ስለ ሲትኮም ድራማ ምንነት ማሳወቅ፣ ስለ ሲትኮም ድራማ ባህሪያት ማሳወቅ እና "አለሜ" ሲትኮም ድራማ ከሲትኮም ድራማ ባህሪያት አንፃር ምን

እንደሚመስል በመተንተን ደካማ እና ጠንካራ ጎኑን በማሳየት የተሻለ ግንዛቤን ማስጨበጥ ነው።

1.3 የጥናቱ ጠቀሜታ

የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ጠቀሜታ

- ሲትኮም ድራማ ማለት ምን ማለት እንደሆን ያሳውቃል
- የሲትኮም ድራማ ባህሪያት እነ ማን እንደሆኑ ያሳያል
- አለሜ ሲትኮም ድራማን ከሲትኮም ድራማ ባህሪያት አንፃር በመመዘን ሲትኮም ድራማን መስራት ለሚፈልጉ አካላት ጥልቅ መረጃን ይሰጣል
- በሲትኮም ድራማ ዙሪያ ለሚሩ ጥናቶች እንደ ግብአትበመሆን ያገለግላል

1.4 ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች

- ሲትኮም ድራማ ማለት ምን ማለት ነው?
- የሲትኮም ድራማ ባህሪያት እነ ማን ናቸው?
- "አለሜ" ሲትኮም ድራማ ከሲትኮም ድራማ ባህሪያት አንፃር ምን ይመስላል?

1.5 የጥናቱ ወሰን

የዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ወሰኑ "አለሜ" ሲትኮም ድራማ ከሲትኮም ድራማ ባህሪያት አንፃር ብቻ መተንተን ነው።

1.6 የጥናቱ ዘዴ

በአንድ የተነሳ ጉዳይ ላይ ጥናታዊ ምርምር አካሄድ የመፍትሔ ሀሳብ ለማቅረብ የሚረዱ መሰረታዊ የሆኑ የምርምር አይነቶች አሉ።

- መጠናዊ ምርምር (quantitative research)

- አይነታዊ ምርምር (qualitative research)

መጠናዊ ምርምር ከስያሜዉ እንድምንረዳዉ መጠንን ገላጭ፥የመረጃዎች፥የሚተነተኑት፥በስታቲካዊ ዘዴ ነው።

ሌላኛው ደግሞ መላምትን ወይም ቲዎርን ተመርኩዞ የሚካሄድ የምርምር አይነት ነው።

"አይነታዊ ምርምር በተወሰነ አንድ ጉዳይ ላይ በማቶኮር ዉስጥ ቁጥር ያላቸዉን የጥናት ተሳታፊዎች በመዉሰድ ያነሳዉን ችግር ከተለያዩ አቅጣጫዎች ይመለከታል"ያለው እንዳወቀ(2006,20)

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍም ተጨባጭ እና ምክንያታዊ እንዲሆን ለማድረግ ይረዳ ዘንድ ከጥናቱ ርእስ ጋር የተዛማጅነት ያላቸውን የተለያዩ መፅሀፎችን በማንበብ እና ድራማዉን በመመልከት እና በመረዳት እንዳስፈላጊነቱ ማጣቀስ የአጥኚው ተቀዳሚ ዘዴ ሲሆን እነዚህንም መረጃዎች ገለፃዊ በሆነ መንገድ የሚያቀርብ በመሆኑ አይነታዊ ምርምር(qualitative research)ዊስጥ ይካተታል።

1.7 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች

አጥኚዉ ይህን ጥናታዊ ጽሁፍ በሚሰራበት ወቅት በዋነኝነት ያጋጠመዉ ችግር ጥናቱን ሊያግዙ የሚችሉ ማጣቀሻ መፅሀፍት እና ትክክለኛ መረጃ አለማግኘት ሲሆን ሌላው ደግሞ ለቃለ መጠየቅ ሰዎችን ለማግኘት አለመቻሉ ነዉ።ነገር ግን ላጋጠሙት ችግሮች በሙሉ ተመጣጣኝ መፍትሄ በመስጠት ጥናቱ ተጠናቆ ሊቀርብ ችሏል።

1.8 የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ በአራት ምዕራፍ የተዋቀረ ሲሆን በምዕራፍ አንድ መግቢያ፣ የጥናቱዳራ፤የጥናቱመነሻ፣የጥናቱአላማ፣የጥናቱ ጠቀሜታ፣የጥናቱዘዴ፣በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ

ችግሮች፤የጥናቱ አደረጃጀት ይቀመጣል፡፡በምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳን ፣የሲትኮምድራማ ምንነት፥ የሲትኮም ድራማ ባህሪያት፥መዋቀር፥ገፅታዎች፥የገፀ ባህሪያት ቅርፆች፥ግጭት፥ጥራት፥የተመልካች ተሳትፎ፥ማህበራዊ አስተያየት፥ተቀምጠዋል፡፡እንዲሁም በምዕራፍ ሶስት የመረጃ ትንተና ቀልድ፥መዋቅር፥ገፅታዎች፥የገፀ ባህሪያት ቅርፆች፥ግጭት፥ጥራት፥የተመልካች ተሳትፎ፥ማህበራዊ አስተያየት፥ተቀምጠዋል፡፡በምዕራፍ አራት ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሃሳቦች ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋዎች፣ዋቢ ጽሁፎች ይገኛሉ፡፡

ምዕራፍ ሁለት

2 ክለሳ ድርሳን

2.1 የሲትኮም ድራማ ምንነት

ድራማ የሠው ለጅ የኑሮ እውነታ አኗኗር አመጋገብ አለባበስ የማህበረሰብ ወይም የሰው ልጅ የአኗኗር ዘይቤ ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ዘውግ ነው።።ሚካኤል የፊልም አፃፃፍ በሚለው መፅሀፍ ላይ ስለ ድራማ እንዲህ አስቀምጦታል ድራማ ሲባል ተናጋሪ ከማለት ይልቅ ተናጋሪው በድርጊት ሲናገር እነደ ማሳየት ማለት ነው።።ሠረቀ ብሎ ከመናገር ይልቅ፤ሲሰርቅ በበእንቅስቃሴ ማሳየት፤ሲበላ በተግባር ማሳየት፤ሲቀና በስሜት ማሳየት ወዘተ...ታሪካችንን የምናሳይባቸው ድራማዊ አቀራረቦች ናቸው።።(2000.ገፅ-22)

ድራማ አብዛኛውን ጊዜ ከንግግር ይልቅ ተግባር የሚያስቀድም የጥበብ ዘርፍ ነው።። የተለያ የድራማ አይነቶች ያሉ ሲሆን ቲቪ ድራማ (TV drama) ሜሎ ድራማ (Melo drama) ሲትኮም ድራማ (sitcom drama) በ ዋንኝነት የሚጠቀሱ የድራማ አይነቶች ናቸው።።ሲተኮም (sitcome) ድራማ የኮሜዲ ዘውግ ያለው የድራማ አይነት ሲሆን ገጸ-ባህሪያቱ ተመሳሳይ ቦታ ላይ የሚኖሩ ተደርገው የሚሳሉና ቃለ ተውኔታቸው የተመረጡ ሳቅን የሚያጭሩ በሳል መሆን አለባቸው።። ኤቫን ስሚዝ የሲትኮም ድራማ ታሪክን በአጭሩ በዚህ መልኩ አስቀምጣዋለችይህ የድራማ ዘውግ አጀማመሩ አ.ኤ.አ በ በ1926 መስከረም ወር በአሜሪካ ሲሆን በሳይመን ሄነሪ(WGN) በተባለ የሬድዮ ቻናል በቺካጎ ሌኖስ ከተማ በየቀኑ ለ15 ደቂቃ በማስተላለፍ ነበር ከዛም በ1928 ወደ ሌላ የራድዮ ቻናል በመዘዋወር እና ስሙን በመቀየር አሞስ እና ኤንዲ በሚል ስያሜ የተዋጣለት መሆን ችሏል ስርጭቱም በሬድዮ ነበር።። በ1947 ለመጀመሪያ ጊዜ(couple sharing a bed) የተባለ ሲትኮም ድራማ ከሬድዮ ስርጭት ከፍ ብሎ በቴሌቭዥን መስኮት ቀረበ ሲሆን የተላለፈው ሀሳብም በ ሴቶች እርግዝና ዙሪያ ነው።። ከዛም በመቀጠል በ1951-1957 (I LOVE LUCY)የተሰኘው ድራማ በCBS የቲቪ ቻናል ለስድስት ተከታታይ ክፍሎች በተዋጣለት መልኩ ለመታየት ችሏል።። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ ሃገራት በብዙ የቲቪ ቻናሎች ሲትኮም ድራማ መታየት ጀምረ።።በዋነኝነት ከሚጠቀሱት ውስጥ አውስትራሊያ(Bless thise house 1970-1980 ABC)፤ካናዳ(kinge of Kensington 1975-

1980)፤ኢንዲያ(yeh jo hai zindagi 1980)፤ሜክሲኮ(El chavodelocho 1971)በዋነኝነት ከሚጠቀሱት ውስጥ ናቸው።(evan smith/1998)

ይህ የድራማ ዘውግ አሁን ላይ የተለመደና በዘመኑ ሰፊ ተቀባይነትና ተወዳጅነት እያተረፈ ያለ ነው። ኦባንግ በአጠቃላይ በአፍሪካ ላይ ያለውን የሲትኮም ታሪክ በዚህ መልኩ አስቀምጦታል በአፍሪካም ያለው የሲትኮም ድራማ ታሪክ የሚገመተውን ያህል ሰፊ ባይሆንም አብዛኛው የድራማ ታሪክ እና ክዋኔ ከሃይማኖታዊ ስርአቶች ተነስተው የሚጻፉ ናቸው።ስለዚህም አለማዊ ለሆነው የድራማ ሀሳብ በተለይም ደሞ ለኮሜዲ ድራማ በአብዛኛው ቦታ የላቸውም ምክንያቱም ደሞ ሃይማኖታዊ ሃሳቡን ለማስተላለፍ ብቻ ስለሚሰሩ በተጨማሪም በአፍ የሚነገር ቃለ-ተውኔት(orale dialogue)ስለሚሰሩ እንዲሁም በአውሮፓውያን ቀኝ ከተያዙ በኋላ ከዛ በፊት የነበረው የአፍሪካ ድራማ እውቅና እንዳይሰጠው በመደረጉ ነው። (obang/2008)

በሃገራችን የመጀመሪያው ተከታተይ ሲትኮም ድራማ ተብሎ የሚጠራው በEbs መዝናኛ ዘውትር ቅዳሜ ማታ 3፡00 ላይ የሚቀርበው ቤቶች ድራማ ሲሆን ከሱ በኋላ ግን ብዙ አይነት ሲትኮም ድራማዎችን በተለያዩ የቴሌቭዥን ቻናሎች ላይ ልንመለከት ችለናል ለምሳሌ፦ ደንብ አምስት፣ምን ልታዘዝ፣ዘጠነኛው ሺ፣አለሜ በዋነኝነት የሚጠቀሱ ናቸው።ሚካኤል የፊልም አፃፃፍ በሚላው መፅሀፉ ላይ ስለ ሲትኮም ደራማ በዚህ መልኩ ገልፆታል ይህ የድራማ አይነት ከድርጊት ይልቅ ቃለ-ተውኔት ይበዛዋል በተጨማሪም የተመልካች ሳቅ በመቅረፀ ድምጽ ተቀርጾ ከሚያስቀው ድርጊት እና ቃለ-ተውኔት ጋር ይለቀቃል።ይህ ሂደት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የመጣ ሲሆን የመጀመርያው ሂደት ድራማ ሲሰራ ተመልካች(audienc) እየተመለከተውና በሳቃቸው እያጀቡ የሚከተሉበትን የነበረ ሲሆን ከላይ እነደተጠቀሰው በጊዜ ሂደት ለውጥ እየተደረገ መሻሻል እየታየበት መምጣቱን ቀደምት ጥናቶች ያመለክታሉ (sitcom)ሲትኮም (situation comedy) ከሚለው ምህጻረ ቃል የተገኘ ሲሆን ከመድረክ ኮሜዲ ድንገታይ ኮምዲ(standup comedy)ፍጹም የተለየ ነው።(ሚካኤል /2000)

ይህ ማለት ሲትኮም ታሪኩ ተከታታይነት የሌለው ቢሆንም ገጸ-ባህሪያቱ ሳይለዋወጡ ከመጀመርያው እስከ መጨረሻው ይዘልቃሉ። (writing television sitcomes) በሚለው መጽሃፍ እንደተቀመጠው ‹‹ሲተኮም በእያንዳንዱ ክፍል ርዕስ ጉዳይ ያለፈውን እና የሚመጣው ተያያዥነት የለውም የግድ ተያያዥ እንዲሆንም አይጠበቅም።››(evan s.smith/2002)

ይህ የሆነበት ምክንያት የህይወት ገጠመኝ ማህበራዊ ክስተቶች በመጠቀም ታሪኩን በየክፍሉ የሚቀይር በመሆኑ ነው።እያንዳንዱ ክፍል የተለየ ርዕስ ይዞ ይነሳል እነዲሁም ወጥ ታሪክ የለውም በዚ ምክንያት ተመልካች ያለፈውን ክፍል ማስታወስ አይጠበቅበትም።ገጸ-ባህሪያቱም ትንሽ በመሆናቸውም ለዕውቂያ የሚፈጅት ጊዜ የለም በተጨማሪም አብዛኛው ታሪክ አነድ ቦታ ላይ የሚያጠነጥን እና ለሚፈጠሩት ክስተቶች በሙሉ መቼቱ የተመቸ መሆን አለበት::ለምሳሌ፡-የመኖሪያ ቤት,ሆስፒታል,ትምህርት ቤት,ካፍቴሪያ,ሆቴል,ፖሊስ ጣቢያ... የመሳስሉትን እንደ ቋሚ መቼት ልንጠቀምባቸው እንችላለን።

በተጨማሪም በሲትኮም ድራማ የሚገኙ ባህሪያት ምን መሆን እንዳለባቸው ሚካኤል እንደሚከተለው ተቀምጧልመቼቱ በአብዛኛው ወቅታዊ እና ዘመናዊ መሆን አለበት።። ሌላው በእያንዳንዱ ሁለት ወይም ሶስት ክፍል ወጥ ገፀ-ባህሪያቱ መታየታቸው ግድ ነው። ይህ የድራማ አይነት በአብዛኛው ዋና ገፀ-ባህሪያቱ ወንዶች ናቸው። ዋና ገጸ-ባህሪያቱ የሚቃረኑት ከማህበራዊ,ፖለቲካዊ,ባህላዊ,ኢኮኖሚያዊ,እና ሀይማኖታዊ ገዢ ህግጋት ጋር ሳይሆን ህግጋቱን ከሚያመነጩት ሰዎች ጋር ነው።ሌላው ገንዘብና ማህበራዊ ትስስር ብቻ በቂ አደለም እየጠፉ ነው ብለው የሚያምኑበትን ማንኛውንም ማህበራዊ ዕሴት ለመመለስ ለማደስ የሚጥሩና የሚሞክሩ ናቸው።(ሚካኤል/ገፅ 113/2000)

ይህም ማለት በማኛውም የሲትኮም ድራማ ውስጥ ከላይ የገለጽናቸው ባህሪያት ሊኖሩ ይገባል።

2.2 የሲትኮም ድራማ ባህሪያት

2.2.1 መዋቅር

- **ትዕይንት ቅርፀት**

ሲትኮም በተለምዶ ትዕይንታዊ መዋቅርን ይከተላሉ፣ እያንዳንዱ ክፍል ራሱን የቻለ ታሪክ በሚያቀርብበት ጊዜ አጠቃላይ ጭብጦችን እና የገጸ ባህሪን ለማዳበር አስተዋፅዖ ያደርጋል፣ ሲትኮም ድራማ በሚታይበት ጊዜ በእያንዳንዱ ክፍል ዉስጥ የተለያዩ ጭብጦች ስለሚታዩ ትእይንቶች አጓጊ እና ተወዳጅ ሆኖ እንዲዘልቁ አስተዋጽኦ ያደርጋል።

- ተደጋጋሚ ገጸ-ባህሪያት

"በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ አንድ አይነት ኮር ተዋንያን ቀርበዋል, ይህም የመተዋወቅ እና ቀጣይነት ስሜት ይፈጥራል"evan s Smith/1998)

በእያንዳንዱ ክፍል ዉስጥ የምናያቸው ገፀባሕርያት የተደጋገሙ እና በየ ክፍሉ የማይቀያየሩ ሲሆን ይሄም ተመልካቹ ተዋናዮችን ለማወቅ እና ስሜቱንም ሰቅሶ ለመያዝ ጠቃሚ ሆኖ ይታያል።እንዲሁም ተዋናዮቹ እርስ በራሳቸው የመተዋወቅ እና ስሜታቸውን ለመጋራት እጅጉኑ ጠቃሚ ሆኖ ይታያል።

2.2.2 ቀልድ

- በገፀ ባህሪይ የሚመራ ቀልድ

"በሲትኮም ውስጥ አብዛኛው ቀልድ የሚነሳው ከገፀ ባህሪያቱ ስብዕና እና ግንኙነት ሲሆን ብዙውን ጊዜ ጉድለቶቻቸውን ያጎላል"alfred jon/2003)

ብዙ ጊዜ የሲትኮም ድራማ ስንመለከት በእያንዳንዱ ክፍል ዉስጥ ቀልድ እና አስቂኝ ሁነቶችን መመልከት የተለመደ ነው።ቀልዱም የሚፈጠረው ገፀባሕርያቱ እርስ በራሳቸው በሚያደርጉት የቃላት ምልልስ እና ድርጊቶች ናቸው።

- ሁኔታዊ አስቂኝ

"ብዙ አስቂኝ ጊዜያት የገጸ-ባህሪያቱን ምላሽ እና መስተጋብር ከሚያሳዩ የእለት ተእለት ሁኔታዎች የመነጩ ናቸው``Alfred jon /2003)

ሲትኮም ለኮሜዲ እንደ መፈልፈያ ሆነው ያገለግላሉ፣ ይህም ጸሃፊዎች የዕለት ተዕለት ጉዳዮችን በቀልድ እንዲፈትሹ ያስችላቸዋል። አብዛኛዎቹን ሲትኮም ድራማ በምንመለከትበት ሰአት ገፀባሕርያቱ እርስ በርሳቸዉ በሚያደርጉት መስተጋብር ሳቅን ሲጭር እና የሚያነሱት ታሪክም በእያንዳንዱ ሰው በእለት ተእለት ኑሮ ላይ የሚያጋጥሙ በመሆናቸው ተመልካቹ የባለቤትነት ስሜት እንዲሰማዉ ያደርጋል።

2.2.3 ገጽታዎች

- ተዛማጅ ሁኔታዎች

"ሲትኮም ብዙውን ጊዜ እንደ የቤተሰብ ተለዋዋጭነት፣ ጓደኝነት፣ ፍቅር እና የግል እድገት ያሉ ሁለንተናዊ ጭብጦችን ይመረምራሉ፣ ይህም ከብዙ ተመልካቾች ጋር እንዲገናኙ ያደርጋቸዋል"evan s Smith /1998)

አብዛኛውን ጊዜ የሲትኮም ድራማ ጭብጦች የሚያተኩሩት በእለት ተእለት የኑሮ ሁኔታ ላይ በሚያጋጥሙ ነገሮች እና በቤተሰብ:በጓደኛ: በፍቅር ላይ ነው።እንደዚህ መሆኑም የተመልካቹ ቁጥር እንዲጨምር እና ተወዳጅነትን እንዲያገኝ አድርጎታል። "ማህበራዊ አስተያየት- ብዙ ሲትኮም የማህበረሰብ ጉዳዮችን፣ የተዛባ አመለካከቶችን እና ባህላዊ ደንቦችን ለመቅረፍ ቀልዶችን በመጠቀም የማህበራዊ ትችት አካላትን ያካትታል"evan s smith/1998)

አሁን ላይ ያሉ የሲትኮም ድራማዎችን ስንመለከት በማህበራዊ በኢኮኖሚያዊ እንዲሁም በፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ትችትና ቅሬታን ለመሰዘር ሲፈልጉ ቀልዶችን በመጠቀም ሀሳባቸውን ያስተላልፋሉ።

2.2.4 የገጸ-ባህሪያት ቅርሶች

ብዙ ጊዜ ዋና ገፀ ባህሪይ ይህ ገፀ ባህሪ ተዛማጅነት ያለው እና የእለት ተእለት ፈተናዎችን ያጋጥመዋል`ብዙዉን ጊዜ ሲትኮም ድራማዎችን በምንመለከትበት ሰአት ዋና ገፀባህሪዉ የተለያዩ ችግሮች እና ፈተናዎችን ይገጥመዋታል።

ከዋና ገፀ ባህሪያቱ ጋር የሚቃረን፣ ባህሪያቸውን የሚያጎላ እና ወደ አስቂኝ ውጥረት የሚጨምር ገፀ ባህሪ ሌላኛው ሲትኮም ድራማን በምንመለከትበት ጊዜ ከአቀንቃኝ ገፀባህርይ ተቃራኒ ሆኖ የሚሰራው ነው።ይሄም በሚፈጥራቸው ግጭቶች እና ዉጥረቶች በተመልካች ላይ ሳቅን በመፍጠር ተመልካችን ያዝናናል። እንደ አልፈርድ ገለፃ ሲትኮም ድራማ ጠንቋዮችን ያቀርባል እና እንደ አስቂኝ እፎይታ ያገለግላል ሌላኛው ሲትኮም ድራማን በምንመለከትበት ጊዜ የተለያዩ ጠንቋዮች እና እብዶችን በማምጣት ተመልካቹን ማስደሰታቸዉ ነው።(alferd jon(2003)

2.2.5 ግጭት

- የግለሰቦች ግጭት

" በገፀ-ባህሪያት መካከል ያለው ግንኙነት ብዙውን ጊዜ ትረካውን ያነሳሳል፣ ይህም ወደ አስቂኝ ነገር ግን ስሜት ቀስቃሽ ጊዜዎች ይመራል"evan s smith /2003)። ገፀባሕርያት እርስ በርሳቸዉ በሚፈጥሩት ግጭት እና አለመግባባት ተመልካቹን በሀሳብ ሰቅሶ የሚዝ እና ትኩረት እንዲያደርጉ ያረጋል። እንዲሁም አንዱ ገፀባህርይ ከሌላው ገፀባህርይ ጋር በሚያደርጉት አለመስማማት ለድራማዉ ርዝማኔና አልሰለች ባይነት እጅጉኑ ጠቀሜታ አለው።

- ውስጣዊ ግጭቶች

"ገፀ-ባህሪያት ከግል ውጣ ውረድ ጋር ሲታገሉ ይችላሉ፣ ይህም ወደ አስቂኝ ገለጻዎቻቸው ጥልቀት ይጨምራል""evan s smith /2003)።

ገፀባህርያት ከራሳቸዉ ጋር የሚያደርጉት ግጭት ሌላው የሲትኮም ድራማ ባህሪ ነዉ።ገፀባሕርያት በእለት ተእለት በሚያጋጥማቸው ፈተናዎች ላይ አተኩሮ ከራሳቸዉ ጋር የሚያደርጉት መስተጋብር ለተመልካቹ ደስታ እና መዝናናትን ይፈጥራል።

2.2.6 ጥራት

- ደስተኛ ፍጻሜዎች

"አብዛኞቹ ሲትኮም በትዕይንት ክፍል ውስጥ ግጭቶችን በንጽሕና ይፈታሉ፣ ሥርዓትን ወደ ነበሩበት ይመልሳሉ እና ብዙ ጊዜ አወንታዊ መልዕክቶችን ያጠናክራሉ"evan s smith/1998)

አብዛኛውን ጊዜ የሲትኮም ድራማ ባህሪያትን ስንመለከት ፍፃሜያቸዉ በደስታ የሚጠናቀቅ ነው።ገፀ ባህሪያቶቹ የተለያዩ ዉጣ ዉረዶችን አልፎ በመጨረሻም አሸናፊ እና ፍትሀዊ ይሆናሉ።

- የገጸ ባህሪ እድገት

"ከጊዜ በኋላ ገፀ ባህሪያቱ ሊሻሻሉ ይችላሉ፣ ለእድገታቸው አስተዋፅዖ የሚያደርጉ ትምህርቶችን እና የተከታታዩ አጠቃላይ ቅስት"evan s smith/1998

ሌላው ሲትኮም ድራማን ለየት የሚያደርገው ነገር ከጊዜያት በኋላ የገፀ ባህሪ እድገት መኖሩ ነው።ገፀባሕርያቱ በተለያዩ ችግሮች እና ፈተናዎች ካሳለፉ በኋላ እድገታቸው እጅጉኑ እየጨመረ እና የሚያሳዩት ነገር ተወዳጅነቱ እየጨመረ ይሄዳል።

2.2.7 የተመልካቾች ተሳትፎ

- ሳቅ እንደ ምላሽ

"የሲትኮም ቀዳሚ ግብ ሳቅን ማስነሳት ሲሆን በተመልካቾች መካከል የጋራ ልምድ መፍጠር ነው"evan s Smith/1995)እንደ ኢቫን ገለፃ ሲትኮም ድራማ ከተመልካቹ ጋር ግንኙነትን በመፍጠር እና ተወዳጅ የሆነ ገፅታዎችን በማሳየት ተመልካቾችን ያዝናናል።

2.2.8 ማህበራዊ አስተያየት

- ባህላዊ ነጸብራቅ

"ሲትኮም ብዙውን ጊዜ የባህል አዝማሚያዎችን ያንፀባርቃል እና ተጽዕኖ ያሳድራል፣ ይህም ተመልካቾች በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ በአስቂኝ ሁኔታ እንዲሳተፉ ያስችላቸዋል"evan e smith/ 1998

አብዛኛውን ጊዜ ሲትኮም ድራማን በምንመለከትበት ሰአት ባህላዊ የሆኑ ነገራቶችን ያንፀባርቃል እንዲሁም በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የራሱን አስተያየት ይሰነዝራል።በዚህም የተነሳ ተመልካቹ ስለ ወቅታዊ ሁነቶች እዉቀት እንዲኖረዉ እና ተሳታፊ እንዲሆን ያስችለዋል።

2.2.9 ርዝማኔ

የሲትኮም ክፍል አብዛኛውን ጊዜ ከ20 እስከ 30 ደቂቃዎች ይቆያል። ይህ የሩጫ ጊዜ ጸሃፊዎች የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግሮችን ሳይጨምሩ የተመልካቾችን ቀልብ ሊይዙ የሚችሉ ፈጣን እና ሙሉ ትረካዎችን እንዲያቀርቡ ያስችላቸዋል። ገፀ ባህሪያቱን ለማሰስ በቂ ቦታ ያለው ለማዋቀር፣ ለሚነሳ እርምጃ እና ለማጠቃለል በቂ ጊዜ አለ።evan s.smith/1998

ምእራፍ ሶስት

3. የመረጃ ትንተና

3.1 የአለሜ ሲትኮም ድራማ ታሪክ በአጭሩ

አለሜ ሲትኮም ድራማ ሚያጠነጥነው በአለሜ እንግዳ ማረፊያ ዉስጥ የሚከናወኑ ተግባራት እና የሚከሰቱ ክስተቶች ላይ ነው።አለሜ የራሱ የሆነ የአልጋ ማረፊያ ያለው ሲሆን በሱም የተለያዩ እንግዶችን በመቀበል የአልጋ አገልግሎት ይሰጣል።ከአለሜ ጋር የሚኖሩ የተለያዩ ጓደኞች ያሉ ሲሆን አለሜ ከአልጋ ክፍያው በሚያገኘዉ ብር እነዚህን ጓደኞቹን ይረዳል።ከነሱም መሀከል ሰላምይሁን አንዱ ሲሆን እሱም የሆነች ትንሽዬ የስራ መኪና ያለዉ ሲሆን በዛች መኪና በሚያገኘው ብር ቤተሰቦቹን የሚያስተዳድር ነው።ብዉ ጊዜ መኪናዉ ስለምትበላሸበት አለሜን ያስቸግራል።ሌላኛው አለሜ ሲትኮም ድራማ ላይ ያሉት ቃኘዉ ሲሆኑ ስራቸዉም የባህል ሀኪም ናቸው።በስራዉም ብዙም ገቢ ስለማያገኝ ከአለሜ ተደግፎ የሚኖሩ አባት ናቸው።በለጠ ደግሞ ቀብር አስፈፃሚ እና የአለሜ የቅርብ ወዳጅ ነው።ሌላኛዋ በአለሜ ሲትኮም ድራማ ያለቹ ደግሞ ብርቱካን ነች።ብርቱካን የአለሜ እንግዳ ማረፊያ አስተናጋጅ እና የእንግዶቹ ተንከባካቢ ነች።የአለሜ ሲትኮም ድራማ ታሪክ በምንመለከትበት ስአት አለሜ ከሚመጡ ሰዎች ጋር የሚያደርገዉ የእለት ተእለት መስተጋብር እና ሁኔታ እንዲሁም የሰው ልጅ በእለት እለት ቆይታዉ የሚደርስበት ፈተና ወይም ችግር እንዴት መቋቋም እንዳለበት የሚያሳይ ነው።እንዲሁም እያንዳዱ ችግር እና ፈተናዎች የራሳቸዉ የሆነ ትምህርት እንደሚሰጡ የሰው ልጅም በነዚህ ፈተናዎች ተሸንፎ እጅ እንዳይሰጥ ትምህርት የሚሰጥ ነው።

3.2 መዋቅር ወይም ትእይንተ ቅርፀት

ከላይ በምእራፍ ሁለት እንደተመለከትነው መዋቅር ወይም ትእይንት ቅርፀት አንዱ የሲትኮም ድራማ ባህሪ ነው። አለሜ ሲትኮም ድራማ ከመዋቅር ወይም ከትእይንተ ቅርፀት አንፃር ስንመለከት በከፊሉም ቢሆን የሚያሟላ ነዉ። ለምሳሌነት የክፍል አንድ ታሪክ የሚያተኩረዉ የድሮ ታሪካቸዉን እንደመማሪያነት እንጂ እንደ መወቀሻነት እንዳይወስዱት ነው የሚመክረው።በዚህም ክፍል ዉስጥ የሰዉ ልጅ በየቤቱ የራሱ ችግር እንደማይጠፋዉ እና ሁሉም የራሱ የሆነ ፈተና እንዳለው ይገልጻል። ለምሳሌነት ክፍል አንድን እንመልከት

ሰላምይሁን : እንዴት አመሻቹ

አለሜ : እያደርክ ለቅሶ መጣህ ምነው?

ሰላምይሁን: ሚሚሚሚሚ ሚስቱ

አለሜ : እ ምን ሆነች ደግሞ

ሰላምይሁን: ስለ ቅርጫ ያወራቹ መስሎኝ መስሎኝ(ብር እየተመለከተ)ምንድነው ይሄ ብር

በለጠ : ይሄ ብር የቅርጫዉ ነዋ

ሰላምይሁን: እናንተ ትቀልዳላቹ ቅርጫ ይገፍ ካልገባሁ ሚስቱ ምን እንደምትለኝ ታቃላቹ

አለሜ : ምን ትልሀለች

በለጠ: ያው እንደተለመደው ዉጣ ትልሀለች

አለሜ : እሱንማ ለምዶታል ባታበራዉ እኮ ነው አሁን ቅር የሚለው

በለጠ : አሁን በበአል ምድር ታባርሀለች

ሰላምይሁን: ፍቅር ይታገሳል ፍቅር ታጋሽ ነው ፍቅር ሁሉ ቻይ ነው ፍቅር አሳቢ ነው

አለሜ : ይሄ ነው የምትለው ሌላ ምትለዉ ነገር የለህ

ይሄንን ስንመለከት ሰላምይሁን ሚስቱን እጅጉኑ የሚፈራ እና በገባ በወጣ ቁጥር የሷን ጭቅጭቅ እና ንትርክ እንደሰለቸዉ ይናገራል።እንዲሁም የሚነግራቸዉ ሰዎች ራሱ ለነገሩ አዲስ ስላልሆኑ እንደሚያሾፉበት እናያለን።በየጊዜው የሚያጋጥሙ ችግሮችን የሚፈቱበት መንገድ ያሳየናል።ይሄም የሚያሳየን አለሜ ሲትኮም ድራማ የመዋቅር ባህሪ ያሟላ መሆኑን ነው።ለምሳሌነት ሌላ ክፍል ስንመለከት ክፍል 11 ላይ የአለሜ የእንግዳ ማረፊያ ዉስጥ የገቡ አንድ ወንድ እና ሴት እርስ በራሳቸዉ የሚያደርጉት ንትርክ እና ጭቅጭቅ እንመልከት

አለሜ : አንቺ ልጅ ተገላልጠሽ እንደሆነ ተሸፈኚ

እንግዳዉ : ችግር አለ እንዴ

አለሜ : ያዉም ተራራ ሚያክል

እንግዳዉ : መጣች እንዴ?

አለሜ : መጣች ያዉም የምስራች እግዚአብሔር ይመስገን መጥታለች እንግዲህ

እንግዳዋ : በቃ እኔ ልሂድ

አለሜ : የት ነው ምትሄጂዉ አንቺ እዚዉ ነሽ ቁጭ በይ

እንግዳዉ : ወይኔ ወይኔ ወይኔ ኧረ የሆነ ነገር ፍጠሪ

እንግዳዋ : ምን ልፍጠርልህ?

እንግዳዉ : የሆነ ነገር

እንግዳዋ : ምን አባክ ዋሽ አለህ አሁን በዚህ ሰአት ይሄ ይባላል **(ክፍል 11 ከ7 ደቂቃ-9 ደቂቃ)**

ይሄንንም ክፍል ስንመለከት አለሜ እንግዳ ማረፊያ የመጣዉ እንግዳ በሚስቱ ላይ ማግጦ ሚስቱ እንዳወቀችበት ሲያቅ ያዙኝ ልቀቁኝ ሲል ነው።በዚህ የተነሳ አለሜ ድራማ ጭብጦቹ ከማህበራዊ ሂወት ጋር የተያያዙ እና ከእለት ተእለት የሰው ልጅ ገጠመኞች ጋር የተያያዙ መሆናቸዉን ነው።

ተደጋጋሚ ገፀባህርያት ከላይ በምእራፍ ሁለት እንደጠቀስነዉ የሲትኮም ድራማ ተደጋጋሚ ገፀባህርያት በየ ክፍሎቹ እንደሚኖሩ ነው።አለሜ ሲትኮም ድራማ ላይ ይሄን የሲትኮም ድራማ ባህሪ እናገኛለን።ከክፍል አንድ እስከ መጨረሻዉ ክፍል ሰላሳ ስምንት ድረስ የማይቀየሩ ገፀባህርያት ያሉ ሲሆን እነሱም አለሜ,ብርቱካን,በለጠ,እና ቃኘዉ ናቸው።ከዚህም አንፃር አለሜ ሲትኮም ድራማ ሙሉ ለሙሉ በሚባል ደረጃ ተደጋጋሚ ገፀባህሪ የሲትኮም ድራማን ባህሪን ያሚላል።

3.3 ቀልድ

ከላይ በምእራፍ ሁለት እንደተመለከትነው ቀልድ ወይም አስቂኝ ሁኔታን መፍጠር አንድ የሲትኮም ድራማ ባህሪ ነው።አለሜ ሲትኮም ድራማ ሙሉ ለሙሉ በሚባል ደረጃ ይሄን ባህሪ

የሚያሚላ ነው።ለምሳሌ ክፍል አንድን ስንመለከት አንድ አልጋ የሚፈልግ ወጣት ወደ አለሜ እንግዳ ማረፊያ ይመጣና ለአለሜ አልጋ ይጠይቀዋል አለሜም ቁልፍ ከሰጠው በኋላ ልጁም አልጋዉን ለማየት ይሄዳል።

አለሜ: ብርቱካን ብርቱካን

ብርቱካን: አቤት ጋሼ ፈለጉኝ

አለሜ: እንግዲህ ይሄ ልጅ የዛሬ እንግዳችን ነው የጎደለ ነገር ካለ ታሚይለታለሽ

ብርቱካን: እንዴ ጋሼ ምንድነው ማሚላለት እርስ በራሳቸዉ ይሞላሉ እንጂ በመስተግዶ የጎደ ካለ እኔ አለሁ

እንግዳዉ: እ "disturbance"አልፈልግም

ብርቱካን: አሁን የጠየከኝ ነገር ግልፅ አድርገው እኔ እዚህ ቤት ዉስጥ አሁን የጠየከኝ ነገር ከሌለ ጭቅጭቅ አልፈልግም እኔ ጭቅጭቅ ነው ያስጠላኝ

እንግዳዉ: "disturbance" እንዳይኖር

ብርቱካን : እንዴ እየነገርኩህ እዚህ ቤት ያሉትን ተከራዬች አቃቸዋለሁ አልኩህ እኮ እንደዚህ ሚባል ሰው የለም

አለሜ: የለም እንደሱ አይደለም ብርቱካን

ብርቱካን: እ

አለሜ: ይቅርታ አድርግላት ፈረጆች ምን ይሉታል መሠለህ "knowledge shortage"አየሀ የእዉቀት ችግር የእዉቀት ችግር ነው እንጂ ለክፉ አይደለም **"(ክፍል1 ከ 9 ደቂቃ እስከ 10:44 ሰከንድ ድረስ)**

ይሄንን ስንመለከት አለሜ ሲትኮም ድራማ ቀልድ አዘል እና በተመልካቾች ላይ ሳቅ የሚጭር መሆኑን እንረዳለን።በየክፍሎቹ ተመልካቾችን ለማዝናናት የሚጠቀሙባቸዉ መንገዶች እንዲሁም ከተመልካቹ ጋር የሚገናኙ ማህበራዊ ርእሶች የአለሜ ድራማ ተወዳጅነት ይጨምራሉ።ሌላ ምሳሌ ስንመለከት ክፍል ሰባት ላይ አንድ ወጣት ስብሰባ ተጠርቶ መጣና ከብርቱካን ጋር ይገናኛሉ

ብርቱካን ምን እየሰራህ ነው

እንግዳዉ ፎቶዎቹ ሳያቸዉ አልቅስ አልቅስ አለኝ

ብርቱካን ዝም ብለህ ነው እንዴ ምታለቅሰዉ

እንግዳው እንባ መተዳደሪያዬ ነው

ብርቱካን ኧሀ መተዳደሪያህ እንደ ድንኳን ሰባሪ በየቤቱ እየገባህ ማልቀስ ነው መተዳደሪያህ

እንግዳዉ ኧረ አይደለም ስብሰባ ተጠርቼ ነው

ብርቱካን የት እዚህ ይሄ እኮ እንግዳ ማረፊያ ነው

እንግዳዉ አቃለሁ አቃለሁ እሱ

ብርቱካን የኔ ጌታ ተሳስተሀል (ክፍል7,ክ3 ደቂቃ_6 ደቂቃ)

ብርቱካን እና እንግዳው የሚያደርጉት የቃላት ምልልስ በተመልካቹ ላይ ሳቅ የሚጭር እና የሚያዝናና ነው።ቀልድ በተፈጥሮ እያሳቀ ቁም ነገርን የሚያስጨብጥ በመሆኑ አለሜ ድራማ ላይም ይሄንን ባህሪ እንመለከታለን።

በአጠቃላይ አለሜ ሲትኮም ድራማ ከቀልድ አንፃር ሙሉ ለሙሉ በሚባል ደረጃ የሲትኮም ድራማ ባህሪን ያሟላል።

3.4 ገፅታዎች

ከላይ በምእራፍ ሁለት እንደተመለከትነው ገፅታ ወይም ተዛማጅ ሁኔታዎች አንድ የሲትኮም ድራማ ባህሪ ነው።አለሜ ሲትኮም ድራማም በምንመለከትበት ሰአት ጭብጦቹ የሚያቶኩሩት በእለት ተእለት የሂወት ገጠመኝ ላይ በሚገጥሙ ተግዳሮቶች ላይ ነው።ለምሳሌነት ክፍል አንድ ብንመለከት ሰላምይሁን ለአለሜ መጥቶ ሚስቱ እንደምታስቸግረዉ እና የፊለገ ነገር ይዞ ቢመጣ ቤት ዉስጥ መጨቃጨቋ እንደማይቀር የሚያሳዩበት ቦታ ነው።አለሜ እና ቤተሰቦቹ ተቀምጠው እያለ ሰላምይሁን ይመጣና

ሰላምይሁን የቅርጫዉ ጉዳይ የት ደረሰ

አለሜ በሬ ለመግዛት የተሰበሰበው ብር ስላልበቃ አንድ ሙክት በግ እንገዛለን

ሰላምይሁን እናንተ ትቀልዳላቹ እንዴ እኔ ሚስቱ ከቤት ልታባረኝ እኮ ነው

አለሜ ገዛህም አልገዛህም ልትባረር ነው ላንተ ከቤት መባረር ብርቅ ነው እንዴ

ሰላምይሁን እሱማ እዉነትህ ነው

ይሄንን ስንመለከት በየ እለቱ ሰላምይሁን ከሚስቱ ጋር እንደሚጨቃጨቅ ያሳየናል።ሌላው በክፍል አንድ ላይ የምንመለከተው ደግሞ በለጠ የቀብር አስፈፃሚ በመሆኑ በየእለቱ አዳዲስ ችግሮች እንደሚገጥሙት ነው።ቹቹ አለሜ ጋር መጥቶ እዚህ ካንተ ጋር መኖር እፈልጋለሁ ሲለዉ አለሜ አይሆንም ብሎ ሲያባረዉ ቹቹም አባቴ ሞቶ ነው ብሎ ይዋሻል።በዚህ ጊዜ ቃኘዉ እዉነት መስሎት ሲያለቅስ በለጠ ቀብር አስፈፃሚዎችን ይዞ በፍጥነት ይመጣል

አለሜ በለጠ እነዚህ ደግሞ እነ ማን ናቸው?

በለጠ ሰዉ ሞተ ተብሎ ቃኘዉ ደዉሎልኝ ነው የመጣሁት

አለሜ ኧረ በፈጠረህ እነዚህ አያልቅሱ አስቁማቸዉ

በለጠ ስንት ስራ ትቼ መሰለህ የመጣሁት (ክፍል1 ከ29 ደቂቃ-30ደቂቃ)

ይሄን ስንመለከት በለጠ በየ እለቱ እንደ ቀብር አስፈፃሚነቱ አዳዲስ ነገራቶች እንደሚገጥመዉ ነው።ሌላ ምሳሌ ስንመለከት ክፍል ስምንት ላይ አለሜ እና እጣ ሚያዞረዉ የሚያደርጉት መስተጋብር ነው

እጣ አሟሪዉ አለሜ ቡርቱ ነች

አለሜ ምን በግ ግዛ ብላ

እጣ አሟሪዉ አይደለም አለሜ እጣ ይቆርጣል ብላኝ

አለሜ ጥሩ ነው ይሄ ስራ ፈጠራ ጥሩ ነው

እጣ አሟሪዉ ተመቸሆታ

አለሜ በጣም እንጂ ተመቸሁህ ማለት ምንድነው

እጣ አሟሪዉ ያዉ በዉስጥ ገባህ ምናምን አለ አ

አለሜ ዉስጥ ገባሁ የምን ዉስጥ

እጣ አሟሪዉ ይኸዉ አታይም የለሁም ለማለት

አለሜ ምን ትመቸኛለህ ግዛኝ ብለህ ነው የመጣኸዉ

እጣ አሟሪዉ እሱማ አዎ ይሄን የመሰለ በግ

አለሜ አሁን አሳብህ ጥሩ ነው ይሄዉልህ ትናንሽ ሰዎች ትላልቅ ሀሳቦችን እንደሚያስቡ ማሳያ ነህ አንተ (ክፍል8,ከ6ደቂቃ-8ደቂቃ)

ይሄንንም ክፍል ስንመለከት አለሜ እጣ አሟሪዉ በሚሰራው ስራ ሲያደናንቀዉ እና ሀሳቡ ትልቅ እንደሆነ የሚመክርበት መንገድ እንዲሁም ትናንሽ ሰዎች ትላልቅ ሀሳቦችን ማመንጨት እንደሚችሉ የሚያነሳበት መንገድ አለሜ ድራማ የገፅታ የሲትኮም ድራማ ባህሪን እንደሚያሟላ ማሳያ ነው።

እንዲሁም ሌሎችም ክፍሎች ላይ ስንመለከት አለሜ ሲትኮም ድራማ ለጭብጥነት የሚጠቀምባቸዉ ርእሶች ከማህበራዊ ሂወት ጋር የተሳሰረ እና አብዛኛውን ማህበረሰብ ያካተተ ነው።ጭብጦቹ የሚያቶክሩት ከእለት እለት የሰው ልጅ ገጠመኝ ጋር ማለትም ኢኮነሚያዊ ማህበራዊ እና ሌሎች ተዛማጅ ሁኔታዎች ጋር በመሆኑ ማህበራዊነቱ በጅጉኑ ይጨምራል።

በአጠቃላይ አለሜ ሲትኮም ድራማ የገፅታ ወይም የተዛማጅ ሁኔታዎች የሲትኮም ድራማ ባህሪን ያሟላል።

3.5 የገፀ ባህሪያት ቅርፆች

ከላይ በምእራፍ ሁለት እንደተመለከትነው የገፀ ባህሪያት ቅርሶች አንድ የሲትኮም ድራማ ባህሪ ነው። አለሜ ሲትኮም ድራማን ስንመለከት ብዙ ጊዜ አለሜ የእለት ተእለት ፈተናዎችን ያጋጥመዋል።ለምሳሌ ክፍል አንድ ላይ

አለሜ አንዴት ነዉ የበሬ ዋጋ

በለጠ ተወኝ አለሜ ይዋጋል

አለሜ ተዉ ባክህ

በለጠ ለአንድ በሬ የሚጠሩት ዋጋ የአንድ ሀብታም ቀብር ያስፈፅማል

አለሜ በለዉ በለዉ

ይህ የሚያሳየው የኑሮ ዉድነት ፈተና እንደሆነባቸው ነው።አለሜ ሲትኮም ድራማ ላይ በየክፍሉ የሚያነሷቸዉ ችግሮች ከእለት ተእለት የሰው ልጅ ፈተናዎች እና የሰው ልጅ በማህበራዊ በኢኮነሚያዉ እንዲሁም በፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ የሚገጥሙትን ችግሮች እያነሱ የመፍትሔ ሀሳቦችን ያስቀምጣሉ።

ሌላኛው የሲትኮም ድራማ ባህሪ ደግሞ ከዋና ገፀ ባህሪያቱ ጋር የሚቃረን እና በተመልካች ላይ ሳቅን መፍጠር ነው። አለሜ ሲቱኮም ድራማ ላይም ይሄንን ባህሪ እንመለከታለን።ለምሳሌነት ክፍል አንድ ላይ

አለሜ ምን ፈልገህ ነው

ተገልጋይ ፈልጌ

አለሜ ማስታወቂያ አይተህ ነው የገባኸዉ

ተገልጋይ አዎ አይቻለሁ

አለሜ ታዲያ ንገረና

ተገልጋይ ማለቴ ቆንጆ አልጋ ጣፋጭ ጊዜ ለማሳለፍ

አለሜ (እየሳቀ)ኤንደዉ ምን ነካህ አለ ለምን ከፈትን ብለህ ነው

ተገልጋይ ስጡኝ

አለሜ ምን?

ተገልጋይ አይ ማለቴ አልጋዉን አሳዩኝ

አለሜ እሺ(ብሎ ቁልፍ ሲያመጣ)

ተገልጋይ ግን ረብሻ አልፈልግም

አለሜ እሺ

ተገልጋይ ማለቱ ከመንገድ ዳር እኛ ገበያ ሲሆን ደስ ይለናል እና ሰፋ ያለ ክላስ ቢሆን ደስ ይለኛል እናም"ሀኒሙናችን "ስለሆነ ጨረቃ ስትገባ በማታ ማየት እንፈልጋለን

አለሜ በስሱ ነው የምትፈልጉት

ተገልጋይ አዉ በስሱ **(ክፍል አንድ ከ9ደቂቃ-11ደቂቃ)**

አለሜ ሲትኮም ድራማ ላይ የሚነሱ ርእሶች የእለት ተእለት የኑሮ ፈተናዎች ዉጣ ዉረዶች እና ያጋጠሙ ችግሮች እና መፍትሄያቸዉ ላይ ነው።ይሄን ስንመለከት አለሜ ሲትኮም ድራማ የተዛማጅ ሁኔታ የሲትኮም ድራማ ባህሪን ያሟላል።

3.6ግጭት

ከላይ በምእራፍ ሁለት እንደተመለከትነው ግጭት አንድ የሲትኮም ድራማ ባህሪ ነው።አለሜ ሲትኮም ድራማ ላይ የተለያዩ ቦታዎች ላይ ገፀ ባህሪያት እርስ በራሳቸው ሲጋጩ ይታያል። ለምሳሌነት ክፍል ዘጠኝ ላይ አለሜ እና መቶ አላቃ የሚያደርጉት የእርስ በርስ ግጭት ማየት እንችላለን

መቶ አላቃ አለሜ እንዴት ዋልክ

አለሜ ፈጣሪ ይመስገን እንዴት ዋልክ

መቶ አላቃ እንግዲህ በባዶ እጅ ጦርነት መሄድ አይቻል

አለሜ በበድረ ሞከንን እና በከዘራ የመሩ ጦረኞችን እናቅ የለ

መቶ አለቃ የጦር ሜዳ ዉሎዉን ለኛ አትነግረንምን

አለሜ ቢያቁኝ ኖሮ እንዲህ አይሉኝም ነበር

መቶ አለቃ ኧሀ ላንተ ስል በትረ ሞኮንን ይገፍ መምጣት ነበረብኝ ማለት ነው።ከዘራም ሲበዛብህ

አለሜ አይ አይ በሰላም ከሆነ ለምን መድፍስ ይዘዉ አይመጡም

መቶ አለቃ ምነዉ ፀብ ያለዉ አስመሰልከዉ

በዚህ ክፍል የተፈጠረዉን ግጭት ስንመለከት ገፀ ባህሪያቶቹ እርስ በርሳቸዉ የሚያደርጉት ግጭት ለድራመዉ ርዝማኔ እና አልሰላች ባይነት እጅጉኑ ሲጠቅመዉ እንመለከታለን።መቶ አላቃ አለሜ በሚሰራዉ ስራ ሲቀና እና የአለሜ የእንግዳ ማረፊያን ስም ለማጥፋት ጋዜጠኞችን ሳይቀር ሲጠቀም አለሜ ደግሞ ይሄን ሳያዉቅ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲሸወድ ይስተዋላል ከዛም ክስ በመመስረት አለሜ መቶ አላቃን ጥፋተኛ ያስደርገዋል ።ገፀ ባህሪያቶች እርስ በራሳቸዉ የሚያነሱት ግጭት ለአለሜ ድራማ ወበትን ሲጨምሩ እና የተከሰቱ ችግሮችን የሚፈቱበት መንገድ ተመልካቹን አስተምሮ የሚያልፉበት ሁኔታ አለሜ ድራማን ለየት ያደርገዋል።ስለዚህም አለሜ ሲትኮሜ ድራማ የግጭት የሲትኮም ድራማ ባህሪ ያሟላል።

3.7 ጥራት

ጥራት አንድ የሲትኮም ድራማ ባህሪ ሲሆን አለሜ ሲትኮም ድራማ ላይም ይሄ የሲትኮም ባህሪ በጉልህ ይታያል።አብዛኞቹን የአለሜ ድራማ ክፍሎች ስንመለከት ፍፃሜያቸዉ ደስተኛ እና ያማሩ ናቸው። ለምሳሌነትም ክፍል አንድ ብንመለከት መጀመሪያ አካባቢ አለሜ መኝታ ፈልጎ ከሚመጡ ደንበኞቹ ጋር ሲጨቃጨቅ እና ሲነታረክ ይታያል በስተመጨረሻ ግን ተሰባስበዉ በአልን እያከበሩ እና በደስታ ሲያሳልፉ ይስተዋላል።በተጨማሪም ክፍል ሶስት ላይ ስንመለከት ቃኘዉ የአንድን ታካሚ ጥርስ ሲነቅል ተሳስቶ ያላመመዉን ይነቅልና ከዛም ፖሊሶች መጥተዉ ቃኘዉን ለማሰር እና ቤተሰቡ ሲጨነቁ በመጀመሪያ አካባቢ ይታያል መጨረሻ ላይ ግን አለሜ ብርቱካን እና ቃኘዉ አንድ ላይ ተሰብስበው ሲጨፍሩ ይስተዋላል።አለሜ ሲትኮም ድራማ ሙሉ ለሙሉ በሚባል ደረጃ የጥራትን የሲትኮም ባህሪ ያሟላል።

ሌላኛው የሲትኮም ድራማ ባህሪ ደግሞ የገፀ ባህሪያት እድገት መኖር ነው።አለሜ ሲትኮም ድራማ በምንመለከትበት ጊዜ የገፀ ባህሪያት እድገት በጉልህ ይታያል።በየክፍሉ እያተደጋገሙ ሚመጡ የገፀ ባህሪያት የእርስ በርስ ግንኙነት እንዲሁም የግጭት መንስኤዎች አለሜ ሲትኮም ድራማ ላይ የገፀ ባህሪያት እድገት እንዲኖር አድርገዋል።በአጠቃላይ አለሜ ሲትኮም ድራማ የጥራት እና የገፀ ባህሪያት እድገት የሲትኮም ድራማ ባህሪያት ያሟላል።

3.1.7 ማህበራዊ አስተያየት

ከላይ በምእራፍ ሁለት እንደተመለከትነው ማህበራዊ አስተያየት አንድ የሲትኮም ድራማ ባህሪ ነው።አለሜ ሲትኮም ድራማ ላይ ማህበራዊ አስተያየት ስንመለከት ለምሳሌ ክፍል አንድ ላይ አለሜ እና አልጋ ፍለጋ የመጣው ቀጣት ሲያወሩ ተመልካቹ በሳቅ የሚያጅብበት ሁኔታ

እንዲሁም በየ ክፍሉ የሚያነሷቸው ርእሶች ከወቅታዊ እና ማህበራዊ ጉዳዮች ጋር የሚያያዙ ስለሆኑ ማህበራዊ አስተያየት እንዲኖር ያደርጉታል።በየክፍሉ የሚያነሷቸዉ ሀሳቦች ለምሳሌ የኑሮ ዉድነት የድሮ ዘመንን መናፈቅ እና የባለ ትዳሮች ወግ እንዲሁም የመሳሰሉ አይነት ርእሶች ተመልካቹ ወይም ማህበረሰቡ እንዲሳተፍ አንድ መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል።ለምሳሌነትም ከ YouTube ገፃቸው የተሰጣቸዉ አስተያየት ስንመለከት መሳይ የሚባል የዩቱዩብ ተጠቃሚ እንዲህ ሲል ሀሳቡን ሰጥተዋል አለሜ ደስ የምትል ቅንጭብ ያለች ድራማ በእዉነት በፍቅር ነው ማያችሁ። ሌላው የዩቱዩብ ተከታታያቸዉ የሆነቹ ኡሙ የንጉሱ ልጅ እንዲህ ብላ አስቀመጠች ደስ ስትሉ ጋሼ ሞኬ ረጅም እድሜ ከጤና ጋር ተመኘሁ ሁላችሁም ዉድድድድ እድሜና ጤና ይስጣችሁ በዚህ ሰአት በጣም አስፈላጊ የሆነ እያስተማረ የሚያዝናና ፕሮግራም።አለሜ ድራማ የሚያነሳቸዉ ሀሳቦች ከማህበራዊ ሁነት ጋር የተያያዘ ስለሆነ ብዙ ተመልካቾቹ ዘንድ ተወዳጅነትን አግኝቷል።አለሜ ሲትኮም ድራማ የማህበራዊ አስተያየት የሲትኮም ድራማ ባህሪን ያሟላል።

3.9 ርዝማኔ

ከላይ ምእራፍ ሁለት ላይ እንዳሳለፍነዉ የደቂቃዎች አጭር መሆን አንድ የሲትኮም ድራማ ባህሪ ነው።አለሜ ሲትኮም ድራማም አጭር የሲትኮም ድራማን ባህሪ በአብዛኛው ክፍሎቹ ሲያሟላ እንመለከታለን።ለምሳሌነትም ክፍል አንድ ብንወስድ የደቂቃው ርዝማኔ 36 ደቂቃ ሲሆን በዉስጡም ተመልካቾችን ለማዝናናት እና መልእክት ለማስተላለፍ በቂ ሰአት ሆኖ ይታያል።ክፍል ሁለት ስንመለከት ደግሞ ከክፍል አንድ ያነሰ ሰአት የወሰደ ሲሆን ብዛቱም 29 ደቂቃ ነው።የአለሜ ሲትኮም ድራማ ሰአቶች አብዛኞቹን ስንመለከት ከ 29 ደቂቃ እስከ 34 ደቂቃ ይፈጃል ።አለሜ ሲትኮም ድራማ ክፍሎቹ የሚወስዱት ሰአት አጭር ቢሆንም በዚሁ አጭር ሰአት ግን የሚፈልጉትን መልእክት ሲያስተላልፉ እና ተመልካቾችን ሲያዝናኑ ይታያል።

በዚህም ምክንያት አለሜ ሲትኮም ድራማ የአጭር ሰአት የሲትኮም ድራማ ባህሪን በከፊሉ ያሟላል

3.10 ከተመልካች ጋር የቀጥታ ስርጭት መኖር

ከላይ በምእራፍ ሁለት እንደተመለከትነው ከተመልካች ጋር የቀጥታ ስርጭት መኖር አንዱ የሲትኮም ድራማ ባህሪ ነው።ተመልካቾች በቀጥታ እየተመለከቱ እያለ ስሜታቸዉን ማጋራት ማለትም የሚያስቅ ከሆነ ቀጥታ ሳቀቸዉን መስማት እንዲሁም የሚያሳዝን ከሆነ ሀዘናቸዉን

መጋራት አንዱ የሲትኮም ድራማ ባህሪ ነው።በዚህ የሲትኮም ድራማ ባህሪ አንባር አለሜ ሲትኮም ድራማን ስንገመግም አለሜ ሲትኮም ድራማ ባህሪዉን የማያሟላ ሆኖ እናገኝዋለን። ምክንያቱም የሚሰማው ሳቅ ከቀጥታ ከተመልካች የመጣ ሳይሆን ሪከርድ ተደርጎ የተጨመረ ነው። እንዲሁም ተመልካቾች በቀጥታ የሚያዩት ሳይሆን በተለያዩ ሚዲያዎች እየተላለፈ የሚመለከቱት ነው። በዚህም የተነሳ ከተመልካች ጋር የቀጥታ ስርጭት በአለሜ ሲትኮም ድራማ የለም።አለሜ ሲትኮም ድራማ ከተመልካች ጋር የቀጥታ ግንኙነት መፍጠርን የሲትኮም ድራማ ባህሪ አያሟላም።

ምእራፍ አራት

4 ማ ጠቃለያ እና የመ ፍትሔ ሀሳብ

4.1 ማ ጠ ቃለያ

የድራማ ጥበብ ለማሳደግ የተለያዩ ደራሲያን፡ፅሀፊያን፡ተዋንያን፡የዘርፉ ባለሞያዎች የራሳቸው አስተዋጽኦ አድርገዋል።ከተንቀሳቃሽ ምስል የፊልም ኢንደስትሪ ድምፅ እና ምስል አንድ ላይ በማ ዋሀድ እዚህ ደርሷል።ድራማ የአንድ ማ ህበረሰብ ባህል፥እምነት፥አመለካከት፥ከማንፀባረቅ አንፃር ከፍተኛ የሆነ ሚና ይጫ ወታል።በዚህ መሰረት በአለሜ ድራማ ላይ የተደረገ ጥናታዊ ፅሁፍ ከሲትኮም ባህሪያት አንፃር ጥሩ እና መጥፎዉን ተመልክቶ የመፍትሔ ሀሳብ እንደሚከተለዉ አስቀምጧል። አለሜ ድራማ ሙሉ ለሙሉ በሚባል ደረጃ የሲትኮም ድራማ ባህሪያትን አሟልቷል።

ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው

1. Sitcome origrnated on radio but today are mosetely founde on television.
2. Sitcom is not releated to the past and the subject of each section.
3 Sitcom drama, often referred to as "dramedy," is a genre that blends elements of both sitcoms (situational comedies) and drama. It typically features comedic situations and dialogue but also incorporates serious themes, character development, and emotional depth. This genre allows for a balance between humor and poignant storytelling, often exploring complex relationships and personal challenges.
4 A sitcom is a television (TV) comedy show that features the same group of characters on each episode as they find themselves in funny and relatable situations. The setting remains the same each week, but each episode stands alone as characters face a predicament

ዋቢ መጽሃፍቶች

ሚካኤል ልዑልሰገድ። <u>የፊልም ፅሁፍ አጻጻፍ</u>። አዲስ አበባ ፤ ብርሃን እና ሰላም ማተሚያ ቤት ፤ 2006ዓ.ም።

Evan s. smith. Writing Televisione Sitcoms.2002

albert jon.sitcom drama and it's characteristics 2008

dalton.2012

Websites

http//.www,facuity,trinty edu/principle/karjalal htm.

http'// en.wikipidia.org